# የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት

# መመሪያ ቁጥር 11/2003

**ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር**

**ታህሳስ** 2003 ዓ.ም

# የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003

## 1 አውጪው ባለሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 75 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል::

## 2 አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## 3 ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሃረጎች በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና የፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ:: ከዚህ በተጨማሪም በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

1. "ሠራተኛ" ማለት በመንግሥት መስሪያ ቤት በገንዘብ ሰብሣቢነትና ያዥነት ወይም በንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የተሰማራ ተቀጣሪ ሰው ነው::

2. "ዋስ" ማለት ሠራተኛው በመንግሥት ገንዘብ ወይም ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ወይም ኃላፊነቱን በአግባቡ ባለመወጣቱ ምክንያት ለሚደርሰው ጉድለትና ጥፋት

ኃላፊ በመሆን የጎደለውን እና/ወይም የጠፋውን ገንዘብ እና/ወይም ንብረት ለመተካት በመስማማት የዋስትና መያዣ በመተማመኛነት የሚያቀርብ/የሚያሲዝ ሰው ነው፡፡

3. "የዋስትና መያዣ" ማለት ሠራተኛው ለተሰጠው የመንግሥት ሃብትና ንብረት ተጠያቂ ለመሆን ሠራተኛው ራሱ/ዋሱ በመተማመኛነት የሚያቀርባቸው በሕግ ስልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጡ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታን፣ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርን፣ የመኪና ሊብሬን እና የመሳሰሉትን የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዶች ያካትታል፡፡ ሆኖም በደመወዛቸው ዋስትና ዋስ የሚሆኑ ሰዎች የወር ደመወዛቸው 2000 /ሁለት ሺህ ብር/ና ከዚያ በላይ መሆኑንና ከዚህ በፊት በደመወዛቸው ዋስትና ለሌላ ሰው ዋስ ስላለመሆናቸው ከሚሰሩበት የመንግሥት መስሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት የሚያመጡት የጽሁፍ ማስረጃ/የማረጋገጫ ሰነድ እንደዋስትና መያዣ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

## 4 የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 የመንግሥት መስሪያ ቤት ተብለው በተመለከቱት ሁሉ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 5 የመመሪያው ዓላማ

የመንግሥት ገንዘብ እና/ወይም ንብረት ለመጠበቅ ኃላፊነት ከተሰጣቸው ሠራተኞች ጋር በተያያዘ በመንግሥት ገንዘብና ንብረት ላይ ለሚደርስ ጉድለት ወይም ጥፋት ኃላፊነትን በመውሰድ የጠፋውን እና/ወይም የጎደለውን ገንዘብ እና/ወይም ንብረት እንዲተካ/ እንዲመለስ የሚያስችል የዋስትና ሥርዓት ማቋቋም ነው፡፡

## 6 የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ኃላፊነት

ማንኛውም የመንግሥት መስሪያ ቤት፡-

1. በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር እና የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጆች እና እነዚህን አዋጆች ለማስፈፀም በወጡ፣ ደንቦች እንዲሁም መመሪያዎች ስለመንግሥት ገንዘብና ንብረት አጠባበቅ፣ አመዘጋገብና አያያዝ፣ ስለወጪ አከፋፈልና ጥቃቅን ወጪዎች የተወሰነ ገንዘብ እንዲሁም በግዥ ላይ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በገንዘብ ያዥነትና ሰብሣቢነት ወይም ንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሰራተኞች ሁሉ ለተሰጣቸው ኃላፊነት የሚሆን ዋስትና ወይም ተያዥ እንዲሰጡ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2. በሠራተኛው ወይም በዋሱ የሚሰጠው የዋስትና መጠን በሠራተኛው ኃላፊትና ዋስትናው በመቀጠር ችሎታው ላይ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት በዋስትናው ውል ይወሰናል፡፡

3. ለሠራተኛው የተያዘው ዋስትና እንዲቋረጥ/ቀሪ እንዲሆን የሚያደርጉ ሁኔታዎች አለመፈጠራቸውን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ አለበት፡፡

4. ሠራተኛው/ዋሱ ያቀረበው የዋስትና መያዣ የሚወክለው ንብረት ይገባኛል ባይ የማይቀርብ እና እግድ ያልተጣለበት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲቀርብ የመጠየቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

5. ሠራተኛው/ዋሱ ንብረቱን በዋስትና ለማስያዝ የተስማማበት ውል በሕግ የፀና እንዲሆን የውሉ ሰነድ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት እንዲረጋገጥና እንዲመዘገብ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

## 7 የሠራተኛው ግዴታ

1. በገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት ወይም በንብረት ያዥነት ወይም በጥበቃ ሥራ ላይ የሚመደብ ማንኛውም ሠራተኛ ዋስትና ማቅረብ አለበት፡፡

2. ማናቸውም የዋስትና መያዣ እግድ ያልተጣለበትና ይገባኛል ባይ የማይቀርብበት መሆኑን ለማረጋገጥ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

3. ሰነዱ ህጋዊ ባይሆን፣ በተጭበረበረ መንገድ የተገኘ በማስመሰል የተዘጋጀ ሆኖ ቢገኝ በአስተዳደር ከሚወሰደው እርምጃ በተጨማሪ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

4. በንብረቱ ወይም በደመወዝ ዋስትና ዋስ የሆነ ሰው በዋስትና ያቀረበው ዋስ ዋስትናውን ለማንሳት ወይም ለመሰረዝ ጥያቄ ሲያቀርብ፣ ሠራተኛው ምትክ ዋስ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡ የቀድሞው ዋስ ጥያቄም በሠራተኛው እጅ ያለ ገንዘብ/ንብረት ተመርምሮ ዕዳ መኖር/አለመኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ ሠራተኛው ጉድለት ያለበት ከሆነና ሠራተኛው ጉድለቱን ካልሸፈነ ከ30 /ሰላሣ/ ቀናት ባለበለጠ ጊዜ ውስጥ ሂሣቡ በመስሪያ ቤቱ የውስጥ ኦዲት ተመርምሮ እንዲቀርብ በማድረግ ይህንን ጉድለት ዋሱ እንዲሸፍን ተደርጎ ጥያቄው ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም መስሪያ ቤቱ አስቀድሞ ሰራተኛው ጉድለቱን እንዲሸፍን ሳይጠይቅ በቀጥታ ዋሱን እንዲከፍል/እንዲመልስ የማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

5. ሠራተኛው የተረከበውን ማንኛውንም የመንግሥት ንብረት ለተጠቃሚዎች አስፈላጊ አፈጻጸሞችን በማሟላት እስከሚያስረክብ ድረስ ለሚደርሰው ጉዳት፣ ጉድለትና ጥፋት ሁሉ ተጠያቂ ነው፡፡

## 8 የዋስ ግዴታ

1. በመንግሥት መስሪያ ቤት ለአንድ ሠራተኛ ዋስ ለመሆን ፈቃደኛ የሚሆን ሰው ንብረት ወይም የመንግሥት ደመወዝ ያለውና ንብረቱን ወይም ደመወዙን በዋስትና ለማስያዝ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ረቂቅ በተመለከተው መሠረት ሙሉ ስምምነቱን መስጠት ይኖርበታል፡፡

2. ሠራተኛው የገንዘብ ጉድለት ቢያደርስ ወይም ይዞ ቢጠፋ፣ ንብረት ቢያጎድል፣ ጉዳት ወይም ብልሽት ቢያደርስ በመንግሥት ኃብት ላይ ለሚደርሰው ማናቸውም ጥፋት ሙሉ ተጠያቂ በመሆን እንደ ጥፋቱ መጠን ያስያዘው ንብረት ተሸጦ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

3. ዋሱ ለዋስትና የሚያቀርበው ማናቸውም የዋስትና መያዣ እግድ ያልተጣለበትና ይገባኛል ባይ የማይቀርብበት መሆኑን ለማረጋገጥ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

4. ሠራተኛው/ዋሱ የሚያቀርበው የዋስትና መያዣ በውል ምዝገባና ሰነዶች ማረጋገጫ ጽህፈት ቤት እንዲመዘገብና የዋስትና ግዴታው እስኪቋረጥ በሚመለከተው መስሪያ ቤት ተከብሮ የሚቆይ እንዲሆን መስማማት አለበት፡፡

## 9 ሊቋረጥ/ቀሪ ሊሆን የሚችልባቸው ሁኔታዎች

1. ሠራተኛው ከገንዘብ ያዥነት ወይም ገንዘብ ሰብሣቢነት ወይም ንብረት ያዥነት ወይም ጥበቃ ሥራ በመነሳቱ፣ ሥራ በመልቀቁ በእጁ የሚገኘውን የመንግሥት ሀብት ያለምንም ጉድለት ሲያስረክብና ለዚሁም የማረጋገጫ ሰነድ ሲቀበል፣

2. በዋስትና የተያዘው ንብረት ለሌላ ሥራ በመንግሥት ተፈልጎ የዋሱ የባለቤትነት መብት ቀሪ ሲሆን፣

3. የተያዘው ንብረት በአደጋ ከጠፋ ወይም ተበላሽቶ ዋጋ ካጣ ወይም ንብረቱ ተሰርቆ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ አለመገኘቱ በፖሊስ ከተረጋገጠ፣

4. ዋስ የሆነው ሰው ዋስትናው እንዲወርድለት ካመለከተ በአንቀጽ 7/4 የተመለከተው ሲሟላ፣

5. በዋስትና የተያዘው ንብረት በእርጅና ዋጋውን ካጣ፣

6. ዋሱ ወይም ሠራተኛው ከሞተ፣ ሆኖም ሠራተኛው ከመሞቱ በፊት ንብረት ወይም ገንዘብ ያጎደለ ከሆነ ዋሱ በኃላፊነት ከመጠየቅ ነጻ አይሆንም፡፡

## 0 የማስታወቅ ወይም የመተካት ግዴታ

1. ሠራተኛው ከገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት፣ ንብረት ያዥነት ወይም ጥበቃ ሥራው ሳይነሳ ዋስትናው ከላይ በአንቀጽ 9/2-6/ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ቢቋረጥ፣ በምትኩ ሌላ ዋስትና የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
2. አሰሪው መስሪያ ቤት የመስሪያ ቤቱ ሠራተኛ በሌላ መስሪያ ቤት ለሚገኝ ሠራተኛ ዋስትና ገብቶ ከሆነና ሠራተኛው የሚሠራበትን መስሪያ ቤት ከለቀቀ ዋስትና ለሰጠበት መስሪያ ቤት ሥራውን ስለመልቀቁ የማሣወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 01 ዋስ ማቅረብ ያለመቻል

በተመሣሣይ ደረጃ በዝውውር ለገንዘብ ያዥነትና ሰብሳቢነት፣ ንብረት ያዥነት ወይም ጥበቃ የሥራ መደብ ላይ እንዲመደብ የተደረገ ወይም ዋስ በማቅረብ ከእነዚህ የሥራ መደቦች ላይ ሲያገለግል ቆይቶ የዋስትናው ውል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 በተዘረዘሩት ምክንያቶች የተቋረጠ ሠራተኛ ዋስ ወይም ምትክ ዋስ ለማቅረብ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን መስሪያ ቤቱ የተረዳ እንደሆነ ሠራተኛው ያለውን ብቃት ከግምት ውስጥ በማስገባት ዋስትና እንዲያቀርብ በማይገደድባቸው የሥራ መደቦች ላይ መድቦ ሊያሰራው ይችላል፡፡

## 02 መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከታህሳስ 1 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ሱፍያን አህመድ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር

# ለመንግስት ሠራተኞች የተሰጠ የዋስትና ውል

ይህ የዋስትና ውል በ _______________________________________
ዚህ በኋላ "ዋስትና ተቀባይ" ተብሎ በሚጠራው አድራሻ_________________
___ እና በአቶ/ወ/ሮ/ወ/ት ____________________ ከዚህ በኋላ "ዋስ" ተብሎ በሚጠራው አድራሻ ክ/ከ _________ ወረዳ _____ የቤት ቁጥር _________ ስልክ _________ መካከል ዛሬ _________ ቀን 200___ ዓ.ም በአዲስ አበባ ተደረገ።

## አንቀፅ 1
## የውሉ መሠረት

ይህ የዋስትና ውል "የፌደራል መንግስት የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003" በሚያዘው መሠረት የተዘጋጀ ነው።

## አንቀፅ 2
## የውሉ ዓላማ

በዚህ ውል አንቀጽ 1 በተጠቀሰው መመሪያ መሠረት ዋስ በሚያስፈልጋቸው የሥራ መደቦች ላይ ሠራተኞች በቅጥር ወይም በዝውውር ወይም በዕድገት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ሲመደቡ ዋስ ወይም በሠራተኛው እና በቀጣሪው የመንግስት መስሪያ ቤት መካከል የሚደረግ ውል ሲሆን ሠራተኛው በ ________________________የሥራ መደብ ተቀጥሮ ሲሰራ ከስራው ጋር በተያያዘ ለተረከበው የመንግስት ገንዘብ ወይም ንብረት ወይም የጥበቃ ኃላፊነት ለሚደርሰው ጉድለት እና/ወይም ጥፋት ዋሱ ከሠራተኛው ጋር በተናጠልም ሆነ በጋራ ኃላፊ እንዲሆንና የጎደለውን ወይም የጠፋውን ገንዘብ እና/ወይም ንብረት እንዲከፍል/እንዲመልስ ለማስቻል ነው።

# አንቀፅ 3

## የዋሱ መብትና ግዴታዎች

**3.1** መብቶቹ

**3.1.1** ዋስ ዋስትና የተገባለት ሠራተኛ ላይ ዕምነት ቢያጣ ወይም በሌላ ምክንያት ተያዥነቱ እንዲነሳለት መጠየቅ ይችላል። ሆኖም ዋስ የሆነለት ሠራተኛ ያጎደለው ወይም ያጠፋው ገንዘብ ወይም ንብረት መኖሩ ከተረጋገጠ ግዴታውን ሣይወጣ ዋስትናው ቀሪ አይሆንም።

**3.1.2** ዋስ የሆነለት ሠራተኛ የተረከበውን ገንዘብ ወይም ንብረት በሙሉ ሲያስረክብ እና ምንም ዕዳ እንደሌለበት በቀጣሪው መስሪያ ቤት ሲረጋገጥ ከግዴታው ነፃ ይሆናል። የዋስትና ውሉም እንደተሰረዘ ይቆጠራል።

**3.1.3** ዋስ ያስያዘው የዋስትና መያዣ የሚወክለው ንብረት የሚያወጣው ዋጋ እንዳለ ሆኖ በዚህ ውል አንቀፅ 4 ከተገለፀው የገንዘብ መጠን ቢበልጥም የዋስ ግዴታ በዚህ አንቀጽ በተገለጸው የገንዘብ መጠን ብቻ የተወሰነ ነው።

**3.2** ግዴታዎቹ

**3.2.1** ዋስ ሠራተኛው በተመደበበት የሥራ መደብ ተቀጥሮ ሲሰራ ከስራው ጋር በተያያዘ በተረከበው ወይም በሚጠብቀው የመንግስት ገንዘብ እና/ወይም ንብረት ላይ ለሚደርሰው ጉድለት ወይም ጥፋት ዋሱ ከሠራተኛው ጋር በተናጠል እና በጋራ ኃላፊ በመሆን የጎደለውን ወይም የጠፋውን ገንዘብ እና/ወይም ንብረት ለመመለስ ወይም ለመተካት ተስማምቷል።

**3.2.2** ዋስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3.2.1. መሠረት የጎደለውን ወይም የጠፋውን ገንዘብ እና/ወይም ንብረት እንዲከፍል እና/ወይም እን ዲተካ ከተጠየቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት _____(_________) ቀናትውስጥ

ግዴታውን ካልተወጣ በንዑስ አንቀጽ 3.2.4. በተገለጸው መሠረት በመያዣነት የተሰጠውን ንብረት እንዲሸጥ ተስማምቷል፡፡

**3.2.3** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3.2.2. የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በደምወዙ ዋስትና ዋስ የሆነ ሰው በንዑስ አንቀጽ 3.2.1. መሠረት ግዴታውን ካልተወጣ የ ወር ደምወዙን 1/3 % (አንድ ሶስተኛ) ዋስትናው እስኪሟላ ድረስ በየወሩ እየተቀነሰ እንዲከፈል ተስማምቷል፡፡

**3.2.4** የጠፋውን ወይም የጎደለውን ገንዘብ እና/ወይም ንብረት መመለስ ወይም መተካት ሳይችል ከቀረ በዋስትና የተሰጠው ንብረት ተሸጦ በዚህ ውል አንቀጽ 4 ከተገለጸው የገንዘብ መጠን ሳይበልጥ በጠፋው/ በጎደለው ገንዘብ እና/ወይም ንብረት ልክ ዕዳውን ለመክፈል ተስማምቷል፡፡

**3.2.5** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3.2. የተገለፁት የዋስ ግዴታዎች ሠራተኛው ንብረቱን በማስያዝ በሚገባው ዋስትና ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## <u>አንቀፅ 4</u><br><u>የዋስትናው ገንዘብ መጠን</u>

ዋስ በዚህ ውል መሠረት የሚሰጠው ዋስትና እስከ ብር____________ (_______ ____________________________ ብር) ድረስ ይሆናል፡፡ ለዚህም ዋስ/ ሠራተኛው_________________________________________ አስይዟል፡፡

## <u>አንቀፅ 5</u><br><u>ተፈፃሚ ሕጎች</u>

ይህ የዋስትና ውል እንደተጠበቀ ሆኖ የዋስ እና ዋስትና ተቀባይ መብቶችና ግዴታዎችን ጨምሮ የፌደራል መንግስት የተያዥ ወይም የዋስትና አሰጣጥ

ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 11/2003 እና የፍትሐብሔር ሕግ የዋስትና ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀፅ 6
## ውሉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ውል ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**የተያዥ ማኅደር**

- ስም አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት(_____)______________________________
- አድራሻ፡

  ክ/ከተማ ___________________ ቀበሌ/ወረዳ_________

  የቤት ቁጥር__________ስልክ____________________

- የሚሰራበት መስሪያ ቤት______________________________
- የሥራ መስክ ______________________________
- በዋስትና የተከበረው ንብረት/ደምወዝ______________________________

  በዚህ ውል ድንጋጌዎች መስማማቱን በፊርማዬ አረጋግጣለው

  ፊርማ_____________________

**የተያዥ ባል/ሚስት ማኅደር**

- ስም አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት(_____)______________________________
- አድራሻ፡

  ክ/ከተማ ___________________ ቀበሌ/ወረዳ_________

  የቤት ቁጥር__________ስልክ ____________________

- የሚሰራበት መስሪያ ቤት______________________________

  የሥራ መስክ ______________________________

  በዚህ ውል ባሌ/ሚስቴ ተያዥ በመሆኑ/ኗ መስማማቴን በፊርማዬ አረጋግጣለው

  ፊርማ_____________________

**<u>ተያዥ /ዋስ የቀረበለት ሠራተኛ ማኅደር</u>**

- ስም አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት(_____)______________________________
- አድራሻ፡

ክ/ከተማ ____________________ ቀበሌ/ወረዳ__________

የቤት ቁጥር___________ስልክ ______________________

- የሥራ ክፍል _______________________________
- የሥራ መደብ/ኃላፊነት_______________________________

## <u>ምስክሮች</u>

| <u>ስም</u> | <u>ፊርማ</u> |
|---|---|
| 1. _______________________________ | ______________________ |
| 2. _______________________________ | ______________________ |
| 3. _______________________________ | ______________________ |